# ወጣት ሆይ፤በጉብዝናህ ወራት ሀገርህን አስብ!

**ሰለሞን ሽፈራው 09-23-17**

ሀገራችን ኢትዮጵያ ከዛሬ 10 ዓመት በፊት በከፍተኛ ድምቀት ያከበረችውን የሚሊኒየም በዓል ምክንያት በማድረግ አንድ በወጣትነት ዕድሜ ዙሪያ የሚያጠነጥን የመፅሔት ፅሁፍ አዘጋጅቼ እንደነበር አስታውሳለሁ፡፡ እናም ለዚያ ጥንቅሬ መነሻ የሆነኝን የህሳብ ግብዓት ለማሰባሰብ በተንቀሳቀስኩበት አጋጣሚ አግኝቼ ካናገርኳቸው ወጣቶች ጥቂቶቹ የሰጡኝን አስተያየት ማስታወስ በዚህ መጣጥፍ ለማነሳው ርዕሰ ጉዳይ የሚጠቅም ሆኖ ተሰምቶኛል፡፡ ምክንያቱም ደግሞ ያኔ "ለመሆኑ የወጣትነት ዕድሜ ላንተ (ላንቺ) ምን ማለት ነው?" የሚለውን ተመሳሳይ ጥያቄ ካቀረብኩላቸው ወጣቶች መካከል በተለይም አንዳንዶቹ የሰጡኝ አጥጋቢ ምላሽ ዛሬም ድረስ ከአዕምሮዬ ጓዳ አልጠፋምና ነው፡፡

እንግዲያውስ ያኔ በአፍላ የወጣትነት ዕድሜ ላይ ይገኙ ከነበሩት ተጠያቂዎች አንዱ "ለኔ ወጣትነት ማለት በአጭሩ የመማሪያና የማፍቀሪያ ዘመን ነው" የሚል ምላሽ የሰጠኝ ሲሆን፤ እንዲሁም ደግሞ ሌላኛው ወጣት "ለምሳሌ ይህን ጥያቄህን ቀይረህ እቺ ሀገር የማናት ብትለኝ ኖሮ የኔ መልስ የወጣት ዜጎቿ የሚል ይሆን ነበር" እንዳለኝ አስታውሳለሁ፡፡ በወቅቱ ካናገርኳቸው ወጣት እንስቶች አንዷ ለጥያቄዬ ምላሽ ስትሰጥ ከዚህ እንደሚከተለው ብላ እንደ ነበርም ማስታወስ ይቻላል…

"እንደኔ እንደኔ ይህ አሁን የምንገኝበት የዕድሜ ክልል እንደየሰው አረዳድና አጠቃቀም ሊወሰን በሚችል መልኩ የወደፊቱን የህይወት ጉዟችንን አቅጣጫ ማስያዝ የምንችልበት እጅግ ወሳኝ ምዕራፍ ነው ቢባል ተገቢ ይመስለኛል፡፡ ምክንያቱም ደግሞ እያንዳንዳችን ዛሬ ላይ በእጃችን ያለውን የወጣትነት ትኩስ ሃይል እንዴት አርገን በጥንቃቄ ልንይዘውና በአግባቡ ወደ ጠቃሚ ውጤት ልንቀይረው እንደሚገባ እስካልተረዳን፤ ምናልባትም ዘላቂ ህይወታችንን የሚያበላሽ መሰረታዊ ስህተት እንድንፈፅም የምንገፋፋበት አደገኛ የዕድሜ ክልል ሊሆን እንደሚችል ይታመናልና ነው፡፡ ለአብነት ያህል እንዲህ እንደኔ ገና በ 20ዎቹ መጀመሪያ ላይ የምትገኝ ማንኛዋም ወጣት ሴት አስቀድማ ተገቢውን ጥንቃቄ ካላደረገች በስተቀር፤ እንደምናያቸው አንዳንድ እህቶቻችን ለጊዜያዊ ስሜት ተሸንፋ ባልተፈለገ እርግዝና ምክንያት ልጅ እስከ መውለድና ከዚያም ተስፋ እስከመቁረጥ የሚያደርስ ፈተና ሊያጋጥማት ይችላል፡፡ ለነገሩ እንደዚህ ዓይነቱ በአፍላ የወጣትነት ዕድሜ ላይ ሊያጋጥም የሚችል የህይወት መሰናከል ሴቶችን ብቻ የሚመለከት ጉዳይ አይደለም፡፡ ምንም እንኳን የአደጋው መጠን እኛ ላይ እንደሚጨምር ባያከራክርም፤ ግን ደግሞ ወንዶቹም አያያዙን ካላወቁበት ዘላቂ ህይወታቸው ተሰናክሎ የማይቀርበት ምክንያት አይኖርምና ጠንቀቅ ማለቱ ለሁላችንም ይጠቅማል ባይ ነኝ" (የጥቅሱ መጨረሻ፡፡)

እንግዲህ ከዚህ በላይ ለማስታወስ የተሞከረውን ሀሳብ የሰነዘሩት ሶስት ኢትዮጵያውያን ከተማ አደግ ወጣቶች፤ የወጣትነት ዕድሜን በየራሳቸው መነፅር ያዩበት አግባብ ከሞላ ጎደል ያነሳሁላቸውን ጥያቄ የመለሰ ሆኖ ነበር ለኔ የተሰማኝ በወቅቱ፡፡ ይህን ስልም ደግሞ፤ምንም እንኳን ለሶስቱ ወጣት እንግዶቼ አንድና ተመሳሳይ ጥያቄ አቅርቤላቸው ሳለ እነርሱ ግን ወርቃማውን የዕድሜ ክልል በሚረዱበት ልክ የሚገልፅ ይዘት ላይ የተመሰረተ ልዩነትን ያሳዩ ሊመስለን ቢችልም፤ሁሉም የሰነዘሩት ሃሳብ ትክክልና ሊስተባበል የማይችል እውነት ያዘለ ነው ማለቴ ይሆናል፡፡

እናም ይህ ከዛሬ 10 ዓመት በፊት የተከበረውን የኢትዮጵያውያን የሚሊኒየም 2000 በዓል ተከትሎ ያኔ በጋዜጠኝነት ሙያ ተቀጥሬ አገለግልበት የነበረው የክልላዊ መንግስት ማስታወቂያ፣ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ እያሳተመ በነፃ እደላ ያሰራጨው ለነበረ አንድ መፅሔት ባሰናዳሁት መጣጥፍ ላይ ሶስቱ ወጣት እንግዶቼ ወርቃማውን የሰው ልጅ የዕድሜ ክልል አስመልክተው የየራሳቸውን ሃሳብ የሰጡበት አግባብ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አሁን ሀገራችን ውስጥ ከሚስተዋለው አጠቃላይ የልማት እንቅስቃሴ መካከል አንዱ ስለሆነው ወጣቱን የህብረተሰብ ክፍል ከስራ አጥነት ችግር የሚታደግ ኢኮኖሚያዊ መነቃቃት የመፍጠር ወቅታዊ አጀንዳ ጉዳይ ማንሳት ግድ ይላል ብየ ስለማምን ነው እኔም እንዲህ መንደርደርን የመረጥኩት፡፡ ስለሆነም አሁን በቀጥታ ወደዋናው የዚህ ፅሁፌ ማጠንጠኛ ነጥብ አልፍና የዛሬዋ ኢትዮጵያ ወጣቶች ወርቃማውን ዕድሜያቸውን እንዴት ለእናት ሀገር የህዳሴ ጉዞ ስኬት ሊጠቀሙበት እንደሚገባ የሚያስገነዝብ ሃሳብ ለማቅረብ እሞክራለሁ፡፡

በዚህ መሰረትም፣ ካለፈው 2009ዓ.ም ጀምሮ የኢፌዴሪ መንግስት እስከ አስር ቢሊዮን ብር የሚደርስ ገንዘብ መድቦ የሀገራችንን ወጣቶች የኢኮኖሚያዊ ዕድገቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ያለመ የተዘዋዋሪ ፈንድ አሰጣጥ (አሰራር) ተግባራዊ እየተደረገ ስለሚገኝበት ተጨባጭ እንቅስቃሴ አንዳንድ ወቅታዊ መዳረሻዎችን በማጣቀስ ለማቅረብ ነው የፈለግኩት፡፡ እናም ከዚህ መሰረተ ሀሳብ ጋር በተያያዘ አንዳንድ የሀገር ውስጥ መገናኛ ብዙሃን አሁን ላይ እያስደመጡን ያለው ዜና እንደሚያመለክተው ከሆነ፣ በርካታ የክልል መስተዳደሮች ወጣቶቻቸውን የተዘዋዋሪ ፈንዱ ተጠቃሚ በማድረግ ረገድ የማይናቅ ርቀት ተጉዞዋል ማለት ይቻላል፡፡

ለምሳሌ ያህልም የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል አብዛኛዎቹ ዞኖች፣ቋሚ ስራና የገቢ ምንጭ ያልነበራቸውን ወጣቶች በማህበር እያደራጁ ወደልማት የማስማራቱን መርሐ ግብር ከሞላ ጎደል ያሳኩበት ሁኔታ እንዳለ ደረጀ ጥላሁን የተባለው የኢ.ብ.ኮ. ጋዜጠኛ ሰሞኑን በተከታታይ የዘገበውን ዜና በምንጭነት መጥቀስ የሚቻል ይመስለኛል፡፡ ከዚህ አኳያ ዜናው ሽፋን ከሰጣቸው የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ዞኖችም ደግሞ፣ እንደ ኢሉ አባቦራ፣ ጅማና ጉጂ ዓይነቶቹ ይገኙበታል፡፡ በተለይም የጅማ ዞን አስተዳዳሪ የሆኑት ባለስልጣን ዜናውን ለዘገበው ጋዜጠኛ ‹‹ወጣቶችን በማህበር እየተደራጁ የተዘዋዋሪ ፈንዱን ገንዘብ እንዲወስዱና ወደ ተለያየ የልማት ተግባር እንዲሰማሩ እያደረግን ያለነው ስራ አጥ ዜጎችን ስራ ለማስያዝ ያህል ብቻ አይደለም፡፡ የኛ ዋነኛው ዓላማችን እነዚህ ወገኖች ለራሳቸው ቋሚ የገቢ ምንጭ ከመፍጠር አልፈው ለሌላው ዜጋ በርካታ የስራ ዕድል የሚከፍቱ ወጣት ባለሀብቶች ሲሆኑ ማየትም ጭምር ነው›› ሲሉ የሰጡት ማብራሪያ ልቤን አሙቆታል ማለት እችላለሁ፡፡

በአንዳንድ የደቡብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል ዞኖችና ወረዳዎችም ተመሳሳይ ወጣቱን የህብረተሰብ ክፍል ያማከለ የልማት ንቅናቄ እየተፈጠረ ያለበት ሁኔታ ስለመኖሩ ነው ሰሞነኛው ዜና አክሎ ያመለከተው፡፡ ሌሎቹ የክልል መስተዳድሮችም ቢሆኑ ከፌደራሉ መንግስት አስር ቢሊዮን ብር ላይ የሚደርሳቸውን ጨምሮ የየራሳቸውን ኢኮኖሚያዊ አቅም ያገናዘበ የወጣቶች ልማት ፓኬጅ ቀይሰው ለተግባራዊነቱ ተጨባጭ ጥረት በማድረግ ላይ ናቸው ተብሎ ይታመናል፡፡ በአጠቃላይ ይኼ መንግስት አሁን አሁን ለወጣቱ የህብረተሰብ ክፍል ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ተጠቃሚነት መረጋገጥ እየሰጠ ያለውን ተገቢ ትኩረት ለታዘበ ሰው እቺ ሀገር እውነትም የወጣት ዜጎቿ ናት የሚያሰኝ ይመስለኛል፡፡

ስለዚህም እንደኔ እምነት ከሆነ፣ በዛሬዋ ኢትዮጵያ ነባራዊ እውነታ ውስጥ ከመቸውም ጊዜ ይልቅ ጎልቶ እየተንፀባረቀ ያለው ብሩህ ተስፋና ብርቱ ስጋት የሚፈራረቁበት ድባብ ‹‹ወጣቱ ዜጋ ሆይ በፈርጀ ብዙ የህዳሴ ጉዞ ላይ የምትገኘውን ሀገርህን

አስብ!›› እንድንል የሚጋብዝ ሆኖ ነው የሚሰማኝ፡፡ ምክንያቱም ደግሞ የየትኛውም ልዑዋላዊ ሀገር ቀጣይ ዕጣ ፈንታ የሚወስነው፤ በተለይም ወጣቱ የህብረተሰብ ክፍል ታሪካዊ ሚናውን በአግባቡ ለመጫወት እንዲችል ሆኖ ሲቀረፅና እንደ ትውልድ ሃላፊነት የሚሰማው ወጣት ዜጋ ማፍራት ሲቻል ብቻ እንደመሆኑ መጠን፤ የዛሬዋ ኢትዮጵያ ውስጥ የተጀመረውን የህዳሴ ጉዞ የማስቀጠል ወይም ያለማስቀጠል ጉዳይ፤ በእያንዳንዱ ወጣት ዜጋዋ ጫንቃ ላይ የወደቀ አደራ ነው ሊባል ይችላል፡፡ በግልፅ አነጋገር፤ ያለፉት ኢትዮጵያውያን ትውልዶች የተሻለች ሀገር እንድትኖራቸው ከመሻት በመነጨ የጋራ ህልም ዙሪያ እየተሰባሰቡ ከመታገልና ትግሉ የጠየቀውን ፈርጀ ብዙ መስዋዕትነት ከመክፈል የቦዘኑበት አንድም የታሪክ አጋጣሚ እንዳልነበር ሲታሰብ፤ ዛሬ ላይ ኢትዮጵያ የምትገኝበትን የስር ነቀል ለውጥ ሂደት አያያዙን ሳናውቅበት ቀርተን ለቅልበሳ አደጋ ቢጋለጥ ድምር ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚችል ከወዲሁ መገመት አይከብድምና ነው ‹‹ወጣት ሆይ በጉብዝናህ ወራት ሀገርህን አስብ!›› የሚያሰኘኝ፡፡

ስለዚህ የአሁኑ ኢትዮጵያዊ ወጣት ትውልድ ታሪካዊ ሃላፊነቱን ለመሸከም የሚያስችል ጫንቃ ሊኖረው ይገባል ስንልም እቺ መከረኛ ሀገርና መላው የብሔር-ብሔረሰብ ህዝቦቿ በትላንቱ የጨለማ ዘመን ታሪካቸው እንዳይታለፍ ስላለፉበት ፈርጀ ብዙ ፈተና በቅጡ ከመረዳት የሚመነጭ ማስተዋልን የተላበሰ መልካም ዜጋ ይሁን ማለታችን ነው፡፡ ሲማርም ሆነ ሲመራመር፤ እንዲሁም ደግሞ ጥሮ ግሮ ሀብት ንብረት ለማፍራት ሲነሳና ብሎም የፖለቲካ ፓርቲዎችን ሲደግፍና ሲቃወም ጭምር የእናት ሀገሩን ዘለቄታዊ እጣ ፈንታ በጥሞና እያሰበ ጎጂውን መንገድ ከጠቃሚው የመለየት ብቃት ያለው ኢትዮጵያዊ ወጣት ዜጋ ከመቸውም ጊዜ ይልቅ የሚያስፈልገን ሆኖ ነው ለኔ የሚሰማኝ፡፡ አለበለዚያ የጋራ ጠላታችን የሆነውን ስር የሰደደ ድህነትና ኋላ ቀርነት ታግለን ለማሸነፍ ስንል የምናካሂደው ፈርጀ ብዙ የልማት ንቅናቄ አንዱ ሲገነባ ሌላው የሚያፈርስበት ከንቱ ድካም እንደማይሆን ዋስትና ላይኖረን ነው፡፡ ለማንኛውም ግን እኔ እንደ አንድ የኢትዮጵያንና የኢትዮጵያዊነትን ከፍታ አጥብቆ የሚናፍቅ ዜጋ እነሆ በአፅንኦት ‹‹ወጣት ሆይ፤ በጉብዝናህ ወራት እናት ሀገርህን ከማሰብ እንዳትቦዝን!!›› የሚል አደራዬን እንዲህ አቀርቤያለሁ፡፡

መዓ ሰላማት!